# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 49 ሚያዚያ 15 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ከሁሉም በላይ ደግሞ ሠራዊቱ አያት ቅድመ አያቶቹ በደማቸዉ ያስከበሩትን የኢትዮጵያ ዳር ድንበር እንደ ዋዛ የሚመለከትንና የሚመራውን አገር ዜጎች በውክልና ጦርነት ውስጥ ማግዶ ውድ የሆነ የህይወትና የአካል ዋጋ ካስከፈለ በኋላ ሰለሚቾች የጠየቁትን የህዝብ ተወካዮች "ምንም አያገባችሁም" የሚልን የአገር መሪ ድምፁንና ኃይሉን አስተባብሮ "አንተ ለአገር አታስፈልግም" ማለት መቻል አለበት።

## የታዋቂው የሙዚቃ ንጉስ ጥላሁን ገሰሰ የቀበር ስነስርዓት በዛሬው ዕለት ይፈጸማል

"አውሮፕላን መጣ እየገሰገሰ፣ በዘፈን አንደኛ ጥላሁን ገሠሠ" እያሉ ከዳር እስከ ዳር ያሉ የኢትዮጵያ ህጻናት የሚያወድሱት፣ የኢትዮጵያ ሙዚቃ አፍቃሪዎች



"የሙዚቃው ንጉስ" ብለው የሚጠሩት፣ የእድሜ ገደብ የሌላቸውን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ያተረፈው ዝነኛው ዘፋኝ ጥላሁን ገሠሠ፣ በየኢትዮጵያዊው አእምሮ የሚያቃጭለውን ውብ ድምጹን ይዞ ጥሎን ሄዷል፤ ወደ ወዲያኛው ተሻግሯል። እሁድ ሚያዝያ 11፣ 2001 ዓም በዓለም ዙሪያ ላለን ኢትዮጵያዉያን የሃዘን ቀን ሆናልን አልፋለች።

ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ፥ ከአባቱ ከአቶ ገሠሠ ንጉሴ እና ከእናቱ ከወይዘሮ ጌጤ ጉርሙ መስከረም 17 ቀን 1933 ዓም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። ከአያቱ ጋር ወሊሶ ከተማ ይኖር የነበረው ጥላሁን፣ ራስ ጎበና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማር ነበር የሙዚቃ ፍቅር ልቡን ሰርጾ የገባው። የማዜም ህልሙን ግን እዛ ሆኖ ወደ ተግባር መተርጎም እንደማይችል ሲረዳ፣ የሙዚቃ ፍቅሩን ብቻ ሰንቆ ወደ አዲስ አበባ አመራ።

የአስራ አራት አመት ልጅ እያለ ወሊሶ ከሚገኙት አያቶቹ ቤት አምልጦ አዲስ አበባ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ፣ ውዱ ሙዚቀኛ ጥላሁን ገሰሰ ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ ብርቅዬ ዜማዎቹን በኢትዮጵያውያን ጆሮ ሲያንቆረቁር ቆይቷል። በነዚህ ዓመታት የኛ ብለን የያዝናቸው አያሌ ነገሮች ተራግፈው በየመንገዱ ሲቀሩብን፣ ጥላሁን ግን ማቀንቀኑን ቀጥሎ ነበር። ለካ ሳናውቀው የትዝታችን ባላደራ ኖሯል።

ባለፉት ሰላሳ እና አርባ አመታት፥ በኢትዮጵያችን ብዙ ነገሮች ተልውጠዋል። የህዝባችን የፍትህ ጥማት የቀሰቀሳቸው ለውጦች ህዝብ ባልወከላቸው ሃይሎች እየተቀለበሱ፣ ያለ ህዝብ ተሳትፎ እና ምርጫ ስንት ያልተለወጠ ነገር አለ? ባንዲራችን ስንቴ መልኩ ተለውጧል። ብሔራዊ መዝሙራችንም እንዲሁ። ዛሬ ዛሬማ ይባስ ብለው ከዳተኞች የገዛ አገራችንንም ህልውና ይፈታተኑት ገብተዋል።

የደርጉ አገዛዝ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ የሃገር ፍቅርን በማሰረጽ ስም የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ዘፈኖች ያዘፍን ነበር። ህፃናቱም ጠለቅ ያለው ትርጉም ባይገባቸውም፥ ከልብ በፈለቀ ስምምነት ብጥቅዬ እጃቸውን እያፋጩ፣ እያጨበጨቡ፣ "ባንዲራችን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ፤ አርማችን ነው መለያችን፣ የኢትዮጵያ ያገራችን" እያሉ ይደልቁ ነበር። ይህ እንግዲህ፣ ሁልጊዜ ጠዋት ወደ ክፍል ሳይገባ በፊት መዘመር ያለበትን ብሔራዊ መዝሙር ሳይጨምር ነው። ከጥቂተ ዓመታት በኋላ ግን፣ ባንዲራውም መልኩን ለውጦ መጣ፤ ብሔራዊ መዝሙሩም እንዲሁ።

ታዲያ እንዲህ "ቋሚ ነገር ያሳጣህ" ተብሎ የተረገመ ለሚመስለው ተከታታይ ትውልድ ቀጣይነት ያለውን ነገር ካስታቀፉት ጥቂት ነገሮች ውስጥ የጥላሁን ሙዚቃዎች ዋናዎቹ ናቸው። አያት፣ አባትና ልጅ በጋራ የኔ ዘመን ትዝታ ብለው የሚነጋገሩበት፣ የሃምሳ ዓመት የትዝታ መዝገብ፣ የጥላሁን ገሠሠ ሙዚቃዎች። ነገሮች ሁሉ ልውጥውጥ ሲሉና ትናንት ያመንበትን ዞር ብለን ያጣነው ሲመስለን፣ የጥላሁን ሙዚቃዎች ግን እዛው ሆነው መልክ ቢለዋወጥም እምነታችን ግን እንዳልተነካ ያስታውሱናል።

አዎን፥ ጥላሁን ስለ ሃገር ፍቅር ያዜማቸው ዜማዎች ለዚህ ምስክሮች

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ግዜ

## የተባበሩት መንግስትታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እንደፈረንጆች አቆጣጠር በመጪው ህዳር ወር በኢትዮጵያ ስላለው የሰብዓዊ መብት አያያዝ ለሚያደርገው ግምገማ አምነስቲ ኢንተርናሽናል አስረጂ ሪፖርት አስገባ።

በመጋቢት ወር 1998 ዓም በተባበሩት መንግስታት ዋና ስብሰባ ላይ የሰብዓዊ መብት ጉባኤ እንዲመሰረት ስምምነት የተደረገ ሲሆን፤ በጉባኤው ስርም በየአራት አመቱ የአባል አገራትን የሰብዓዊ መብት ሁኔታ የሚገመግም ሂደት እንዲጀመር ውሳኔ ተላልፎ ነበር። ይህ ዩኒቨርሳል ፔሬዲክ ሪቪው (ዩ.ፒ.አር) የተባለው ሂደት ዋና አላማም አባል አገራት ሰብዓዊ እና ተፈጥሯዊ መብቶችን በሙሉ የማክበር እና ስራ ላይ የማዋል ግዴታቸውን እንዲወጡ ማሳሰብ መሆኑን በኮሚሽኑ ድህረ ገጽ ላይ ከተቀመጠ መረጃ ለመረዳት ተችሏል።

እስካሁን ድረስ በብዙ አባል አገራት ላይ ግምገማው የተደረገ ሲሆን፥ የኢትዮጵያ ተራም በመጪው ህዳር ወር እንደሆነ ታውቋል። በግምገማው ወቅት የተገምጋሚዎቹ አገራት ተወካዮች ቀርበው በየአገሮቻቸው የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ላይ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚጠበቁ ሲሆን፣ ሌሎች ያገባናል የሚሉ ቡድኖች እና ተቋማትም በዛ አገር ላይ አስረጂ ሪፖርት ማስገባት እንደሚችሉ ታውቋል።

በዚህ መሰረትም፥ ታዋቂው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሽናል ሚያዝያ 5፣ 2001 ዓም በኢትዮጵያው አገዛዝ ላይ ሪፖርቱን አስገብቷል። በሪፖርቱ፥ በቅርቡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን (መያዶችን) በሚመለከት ስለወጣው አፋኝ ህግ እና በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ስለሚካሄደው ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ ስጋት እና ነቀፌታውን ገልጿል።

መያዶች ከ10% የሚበልጥ እርዳታ ከውጭ አገር መቀበል አይችሉም የሚለውን ህግ በሚመለከት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያን ያህል እርዳታ ማሰባሰብ በማይቻልበት ሁኔታ ይህ ህግ ብዙዎቹ ቢሮዎቻቸውን እንዲዘጉ እንደሚያስገድዳቸው ያለውን ስጋት ገልጿል። እንደ አምነስቲ ገለፃ፥ በ1991 የጸደቀ የተባበሩት መንግስታት አዋጅ ማንኛውም በሰላማዊ መንገድ ሰብዓዊ መብቶች እንዲስፋፉ የሚሰራ፣ ለስራው ገንዘብ የማሰባሰብ፣ የመቀበል እና የመጠቀም መብት እንዳለው የሚደነግግ ሲሆን፣ ይህ የኢትዮጵያው አገዛዝ ያወጣው ህግ ያንን አዋጅ ይጻረራል።

አምነስቲ በመጨመርም፥ በኦጋዴን እየተካሄደ ስላለው የጅምላ እስር፣ ስቃይ፣ አስገድዶ መድፈር እና ህገ-ወጥ ግድያዎች ስጋቱን የገለጸ ሲሆን፣ እነዚህ ሁሉ ወንጀሎች በገለልተኛ አካል አለመመርመራቸውን አስታውሷል። በኦሮሚያም ኦነግን ይደግፋሉ በሚል በሺዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች በህገ-ወጥ መንገድ ለእስር መዳረጋቸውን እና፣ በህዳር እና ታህሳስ 1998 ብቻ በሺዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞ ተማሪዎች መታሰራቸውን እና የተወሰኑትም መገደላቸውን ገልጿል።

## የመለስ አገዛዝ ባገሪቱ ያሰፈነውን አፈናና ወከባ ፈርተው የሚሰደዱ የመንግሥት ባለሥልጣናትና ባለሙያዎችን ንብረት ለመውረስ የሚያስችል ህግ እየረቀቀ መሆኑ ታወቀ።

ዘረኛውንና አምባገነኑን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ እየከዱ በተለያዩ ሀገራት ጥገኝነት የሚጠይቁ ባለስልጣናትን እና ባለሙያዎችን ንብረት የሚወርስ እና የባንክ ሂሳባቸውን የሚዘጋ ረቂቅ ህግ እየረቀቀ እንደሆነ የታመኑ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ለግንቦት ሰባት የአዲስ አበባ ዘጋቢ ገለጹ። እንደ ውስጥ አዋቂዎቹ ለመንግስት ስራ እና ለተለያዩ ጉዳዮች ከሀገር ከሚወጡ ባለስልጣናት መካከል ጥቂት የማይባሉት በወጡበት መቅረት ወያኔን እንዳስጨነቀው እና ረቂቅ ህጉን ለማውጣት እንዳበቃው ተናግረዋል።

በተዘረፈ የህዝብ ድምጽ በተቋቋመው ፓርላማ ተብዬ በቅርቡ እንደሚቀርብ የሚጠበቀው የሚከዱ ባለስልጣናትን ንብረት የሚወርስ እና የባንክ ሂሳባቸውን የሚያግድ ህግ፣ እንደተለመደው የአለቆቻቸውን ፊት አይተው እጃቸውን በሚያንጠለጥሉ ሆድ አደሮች እንደሚጸድቅ ሳይታለም የተፈታ ነው ተብሎአል።ወያኔ አይን ባወጣ መንገድ ከዘረፈው ከምርጫ 97 ወዲህ በተለይ በርካታ ባለስልጣናት፤ የጦር አለቆች እና ዳኞች ግፈኛውን አገዛዝ መክዳታቸው የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ ዳኛ ወልደ ሚካኤል መሸሻ እና ብርጋድየር ጄኔራል ከማል ገልቹ የሚጠቀሱ ናቸው።

የቀድሞ የአፍዴን ጸሃፊና በምርጫ 97 የፓርላማ ተመራጭ የነበሩት ዶ/ር ጌታቸው ጂጊ፣ የወያኔ ባለስልጣናት እና የጦር ሀላፊዎች አገዛዙን ጥለው የመሄዳቸውን ሁኔታ ከደርግ ዘመን ጋር አመሳስለው <<መንግስቱ ሀይለማርያምን ጄኔራሎቹ አልከዱትም ነበር። እሱ እራሱ ነው ከድቶአቸው የኮበለለው። አሁን የሚታየው በተቃራኒው ነው። መለስን የሚከዱት ጄኔራሎች ናቸው።>> ብለው መናገራቸው ይታወቃል። ዶክተር ጌታቸው ጂጊ እራሳቸውም ፓርላማ ውስጥ አንዳች ነጻነት እንደሌለ እና፤ የመለስ አገዛዝ ዘረኛ እና ገዳይ አገዛዝ እንደሆነ በመግለጽ መክዳታቸውና በጎረቤት ሀገር ጥገኛነት መጠየቃቸው፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ከቤልጅዬም መንግሥት ባገኙት ጥገኝነት በአሁኑ ሰዓት እዚያ እንደሚኖሩ ይታወቃል።

## የመለስ ዜናዊን የአጥፍተህ ጥፋ ሴራ ማምከን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የዜግነት ግዴታ ነው

የመለስ አገዛዝ ወደ ስልጣን ለመውጣትና በስልጣን ለመቆየት ከተጠቀመባቸዉ ውሸቶችና ሴራዎች አንዱ የሃገሪቱን የተለያዩ ዘውጌ ማህበረሰቦች የቋንቋና የባህል ልዩነት በመጠቀም እርስ በርሳቸው ግጭት ውስጥ እንዲገቡ፤ በጥላቻና በጥርጣሬ እንዲተያዩ፤ ተግቶ መስራት ነበር። በተለይ ኦሮሞን ከአማራው በማጋጨት ፍጥጫ ውስጥ ሲወድቁ ወያኔ «የሰላምና የመረጋገት ዋስትና ሰጪ በመሆን ስልጣን ላይ መቆየት፣ ያሻውንም ለማድረግ ይቻለዋል» የሚል እቅድ በ1982 ዓ.ም. መለስ ዜናዊ ስልጣን ከመውጣቱ አንድ አመት በፊት ነድፎ ተለጣፊዎቹንም ብአዴንና ኦሆዴድን በእቅዱ አጥምቆ የመጣ መሆኑን የድርጅቱ ምስጢራዊ ሰነዶች ያስረዳሉ። የብአዴን መሪዎችም የእነዚህ ሰነዶች ይዘት ተቋዳሾች ነበሩ። ወያኔ የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን (ኦነግን) ለስልጣን መወጣጫነት እንዴት እንደሚጠቀምበትና መልሶ እንደሚመታው ባተተበት ይህ የ1982 ምስጢራዊ ሰነድ ላይ «አማራውን ለማሸማቀቅ ኦነግን ማሳበጥ፤ አማራውን በማሸማቀቅ ስልጣናችንን ካጠናከርን በኋላ ኦነግን ማስተንፈስ» የሚል ትንተና ይገኝበታል። ይህ የ1982 ሰነድ ቃል በቃል የተወሰደው አረፍተ ነገር እንደሚለው «ኦነግ ለተወሰነ ግዜ አንደጎማ ይነፋል ይህ ሊያሳስበን አይገባም። የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመን ግን መልሰን እንደጎማ ማስተንፈስ እንችላል» የሚል የእብሪት ሴራ በነመለስ ተደግሶ ነበር ኦነግ ወደ ሽግግሩ መንግሰት የተጋበዘው፣ በኋላም ስልጣንም ተጠቃላ ወያኔ እጅ የገባችው።

ውኸንብር በነበረባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ወያኔ ያሰበው ተሳክቶለት ስልጣኑን ለማጠናከር ቢችልም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ዘውጌ ማህበረሰባት ግን ወያኔ የደገሰላቸውን የጥፋት ወጥመድ አደገኛነት ለመረዳት ግዜ አልፈጀባቸውም። በተለያዩ ግዜያት ወያኔ የደገሰውን ደም የመቀባበት ግብዣ «አንቀበለም» በማለት ከወያኔ በስተቀር የመብታቸው የእድገታቸው የሰላማቸው ጸር እንደሌለ የተረዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ዛሬ አፋሩ፣ ጋምቤላው፣ አማራው፣ ኦሮሞው፣ ጉራጌው፣ ወላይታው፣ ሲዳማውና የተቀሩት የሃገሪቱ ዘውጌ ማህበረሰብ በሙሉ የወያኔን ዘረኛ አምባገነንነት፣ ዘረኛ ዘራፊነት፣ ዘረኛ ሴረኛነት ተረድተዋል። በዘር ማጥፋት ወንጀል የተከሰሰው መለስ ዜናዊ ስለዴሞክራሲና ስለብሄሮች መብት አስከባሪነቱ የሚያወራውን ተረት ተረት የማያዳምጡበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። የዘር ጥላቻ ሳይኖር፣ ህዝብ እርስበሩሱ ሳይተላለቅ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር ፣ በቋንቋ የመጠቀምን፣ ባህልን የማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ብልጽግና ማምጣት፣ የሁሉም አለኝታ መሆን የምትችል በማንም የማትደፈር ነጻ ሃገር መገንባት እንደሚቻል ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ የተረዳው ጉዳይ ሆኗል።

ወያኔ ይህ ህዘብን በዘር ጥላቻ በማፋጠጥ በስልጣን የመቆየት ውጥን እንደማያዋጣዉ ካወቀ በኋላ «ህዝብን በሃይማኖት ጥላቻ አፋጦ መግዛትና መዝረፍ» የሚል እኩይ እቅድ አዉጥቶ እየተንቀሳቀሰ ነዉ። በተለይም በሁለቱ ትላልቅ የሃገራችን እምነት ተከታዮች መሃል የመረረ ጥላቻ ለማስረፅ የሚሰራጩት ፕሮፓጋንዳዎችና የጠብ ጫሪነት ሥራዎች ለዓመታት የምናውቀው የወያኔና የመለስ ዜናዊ አሻራዎች ያሉባቸው ናቸው።

መለስ ዜናዊ በ1997 በሃገር ውስጥ የፈጸመው ጭፍጨፋ የቀሰቀሰውን ዓለም አቀፍ ውግዘትና ሃገራዊ ቁጣ ትኩረት ለማሳት ሱማሌን በወረረበት ወቅት «ኢትዮጵያ የክርስቲያኖች ሃገር ናት» ብሎ ለአንድ የምእራብ የውጭ ጋዜጠኛ መለስ ሲሰጥ ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ወገንተኛነት ተሰምቶት አልነበረም። መለስ የያዘው ንግድ ነውና ከምእራባውያን ገንዘብ እስከተገኘ፣ በስልጣን የሚያስቆይ የመሳሪያ ድጋፍ እስከቀረበለት ድረስ በአንድ ወቅት ለሊቢያው ጋዳፊ የተናገረውን «የእናቱን የመናዊነት» ረስቶ የሃገራችንን የእስልምና ተከታዮች በሃገር እንደሌሉ አድርጎ ቢናገር የሚገርም አይደለም።

አንዱን ተራ ካድሬ ሰደባችሁብኝ በማለት የዜጎችን ጥርስ እንዲያረግፉ ለጸጥታ ሰዎቹ ስልጣን የሰጠ አገዛዝ በሃይማኖት ስም የሰዉ ህይወት ሲጠፋ፤ በሚያስፈራና በሚሰቀጥጥ ደረጃ ቅዱስ በሆኑ መንፈሳዊ ቦታዎች ላይ የክርስትናና የእስልምና እምነቶችን የሚያረክሱ ቆሻሻ ተግባሮች ሲፈጸሙ ዝም ብሎ ማየት፤ እነዚህን የረከሱ ድርጊቶች በአደባባይ በምስልና በድምጽ እንዲቀዱ እድል መስጠት፤ በመለስ ዜናዊና በጓደኞቹ ሆን ተብሎ የሚሰራ ጉዳይ ነው። ቢፈልጉ ኖሮ የመለስ የጸጥታ ሃይሎች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ የሚሰግደውን «የእስልምና ተከታይ ነኝ» ባይንም ሆነ በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በራፍ ነብዩ መሃመድን በባለጌ አፉ አየዘለፈ በቢድዮ እንዲቀረጽ እድል የሰጡትን ባህታዊ ተብዬን ማስቆም አያቅታቸውም ነበር።

ይባስ ብሎ መለስ ዜናዊ የራሱን እኩይ ሥራ «የከሰሩ» ወደሚላቸዉ ፓለቲከኞች ያላክካል። ምርጫ 97 ኢትዮጵያዉያን የዘዉግን ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትንም ድንበር ተሻግረዉ የሚጠቅማቸዉን ፓሊሲ መምረጥ የሚችሉ መሆናቸዉን ያስመሰከሩበት መሆኑን ወያኔ ገና አልተገነዘበም። እንደ እውነቱ ከሆነ በምርጫ 97 የከሰረዉ ወያኔ ነዉ፤ ይህንን ኪሳራ ለመሸፈን የሚችለዉን ሁሉ አድርጓል። አሁን ደግሞ ከሁሉም በላይ አደገኛ የመሰለዉን ካርድ መዟል።

በቅርቡ የአንድነት ፓርቲ «መሪያችን ብርተካን ሚዲቅሳ ትፈታ» ብሎ ባደረገው ሰልፍ ላይ «ተሰላፊዎቹ ሲያስተጋቡት ከነበሩት መፈክሮች መሃከል ‹ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ነች› የሚል መፈክር ሲስተጋበ ነበር» በማለት የመለስ ዜናዊ ዋናው አፈቀላጤ የሆነው አይጋ የተባለው ድረ ገጽ አጅግ ከእውነት የራቀ የውሸት ዘገባ አቅርቧል። ይህ ድረ-ገጽ በወያኔ ገንዘብ በሚንቀሳቀሱ አባላቱ የተደራጀ፣ መለስ ዜናዊም በየግዜው መኮንን በሚል የኢሜል ስም የራሱን ጽሁፍ የሚያሰራጭበት ድረ ገጽ መሆኑን ለምናውቀው፣ አይጋ ሰልፉን በሚመለከት ተሰላፊዎቹ በቃል ይሁን በድሁፍ በማናቸውም መልኩ ያላስተጋቡትን የክርስቲያንነት መፈክር ፈጥሮ በዘገባው ለመከትት ምን እንደገፋፈው ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አያስፈለግም። መመሪያው የመጣው በቀጥታ ከመለስ ዜናዊ ጽ/ቤት ለመሆኑ የወያኔን ማእከላዊነቱ የጠበቀ አሰራር ለሚያውቁ ሁሉ ግልጽ ነው። ይህ የሚይዙት የሚጨብጡት ያጡት መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ሃይማኖትን የፖለቲካ መሳሪያ ለማድረግ መቁረጣቸውን የሚያሳይ ነው።

ይህ የመለስ ዜናዊ የጥፋት ሴራና መዘዙ ምን ሊሆን እንደሚችል ሁሉም የሃገሪቱ ዜጋ ካሁኑ መረዳት መቻል አለበት። የመለስ አገዛዝ በዘር እንድንፋጅ የጠነሰሰውን ሴራ እንዳከሸፍነው ሁሉ ይህንን በሃይማኖት ተከፋፍለን እንድንጫረስ እያጠመደልን ያለውን ሌላ ሴራ ካሁኑ ማክሸፍ መቻል አለብን።

ኢትዮጵያ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ሃገር ብቻ አይደለችም። ቁጥራቸው ጥቂት ይሁኑ እንጂ የራሳቸው እምነቶች ያላቸው ሌሎች ማህበረሰቦች የሚገኙባት ሀገር ናት። ኢትዮጵያን የአንድ ሃይማኖት ሃገር ልትሆን አትችልም። ይኸኛው ሃይማኖት ከእዚህ ይሻላል የሚል የማበላለጥ ጨዋታም የመለስ እኩይ ህልም ማስፈጸሚያ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል። ሁላችንም «ሃይማኖት የግል ነው ሃገር የጋራ ነው» ለሚለው መሰረታዊና እውነተኛ ብሂል ክብደት ሰጥተን ለእምነታችን፣ ለጋራ ሰላማችን፣ ለብልጽግናችን መከበር በጋራ የመለስ ዜናዊ ሴራ ለማክሸፍ መነሳት ይኖርብናል። የእምነት መብቶቻችን የዜጎች የዴሞክራሲ መብቶች እንጅ ማንም አምባገነን በችሮታ የሚሰጠን አይደለም። የእምነት እኩልነት ጥያቄ መስተናገድ የሚችለው የአንዱን መብት ቀምቶ ለሌላው በመስጠት ሳይሆን ሁሉም እምነቶች በእኩልነት ማስተናገድ የሚችሉበት ፍትሃዊ ስርአት በሃገር ሲሰፍን ብቻ ነው። ልክ እንደ ዘውግ የመብት ጥያቄ፣ የሃይማኖት ጥያቄም ከአንዱ መብት ወስዶ ወይም ቀምቶ ለሌላው ወገን አንደሚሰጥ አድርጎ በማቅረብ፣ የአንዱ መብት በሌላዉ ኪሳራ እንደሚሟላ በማድረግ ህዝብ እርስ በርሱ በጠላትነት የሚተያይበትን ሁኔታ ለመፍጠር መለስ የሚፈጽማቸውን ጥቃቅን የሰይጣን ስራዎች ሳይቀሩ በጥንቃቄ በመመርመር «ነቅተንብሃል» ማለት ይገባል። ሀገራችንን ጀሃነብ ሊያደርጋት ቀን ከሌለት የሚሰራውን ዋንኛውን ሰይጣን፣ መለስ ዜናዊን፣ ሁላችንም በአንድ ድምጽ፣ እንደየ እምነታችን በፈጣሪያችን ስም «እርኩስ መንፈስ ውጣ! ውጣ! እርኩስ መንፈስ ከህይወታችን ውጣ! ከሃራችን ውጣ!» ለማለት ቆርጠን እንነሳ።




የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## የሚነዳ ፓርላማና ራዕይ የሌለዉ መሪ!

በአገራችን በኢትዮጵያ የዘመናዊ ፓርላማ አሰራር የተጀመረዉ በ1924 ዓም በቀዳማዊ ኃይለስላሤ ዘመነ መንግስት የመጀመሪያዎቹ አመታት ነዉ። የአፄ ኃይለስላሤ ፓርላማ የህግ መወሰኛና የህግ መምሪያ ተብለዉ የሚጠሩ ሁለት ክፍሎች ነበሩት። በ1966 ዓም የኃይለስላሤ ስርአት በህዝባዊ አመፅ ሲወገድ ፓርላማዉም በአዋጅ ታግዶ ለሚቀጥሉት 14 አመታት እንደተዘጋ ቆየ።ሁለተኛዉ የአገራችን የፓርላማ ታሪክ የተጀመረዉ በ1979 ዓም በደርግ ዘመነ መንግስት ነዉ፤ የደርግ ፓርላማ እንደ አፄ ኃይለስላሤ ፓርላማ ተጠሪነቱም ሆነ አገልግሎቱ ለህዝብ ሳይሆን ለአምባገነኑ ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማሪያም ነበር። ዛሬስ? እንደ ቀድሞዎቹ ሁለት ስርአቶች ዛሬም ኢትዮጵያ ዉስጥ ለጉድ የተጎለተ የይስሙላ ፓርላማ አለ። ይህ ፓርላማ ወያኔ መመሪያዬ ነዉ ብሎ እራሱ ጽፎ እራሱ ባፀደቀዉ ህገ መንግስት አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የአገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን አካል ነዉ፤ በተግባር ግን መለስ ዜናዊ እንዳሻዉ የሚዘዉረዉ የግል መኪና ነዉ። ወያኔ በ1983 ዓም አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ለኢትዮጵያ ህዝብ ከገባቸዉ ቃል ኪዳኖች አንዱ ህዝባዊ ሥርዐት እንፈጥራለን የሚል ነበር፤ የወያኔን ህዝባዊ አለመሆን በሚገባ የተረዳዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን የዉሸት ቃል ኪዳን ሙሉ ለሙሉ ባይቀበልም ከደርግ የባሰ ምን ይመጣብኛል በሚል እምነት ብቻ ላለፉት 18 አመታት የወያኔን ባዶ የተስፋ ቃል ሲጠባበቅ ቆይቷል።

ኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ ዉስጥ እጅግ ከተዋቡና ታሪካዊ ከሆኑ ህንፃዎች ዉስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ፓርላማ ህንፃ ሲሆን እጅግ አስቀያሚና ታሪካዊ ስህተት በየዕለቱ ከሚሠራባቸዉ የአዲስ አበባ ህንፃዎች አንዱ ይሄዉ የፓርላማዉ ህንፃ ነዉ።የኢትዮጵያ ፓርላማ መለስ ዜናዊ ሲናገር ለማጨብጨብ የተፈጠረ በአይነቱ ብቸኛ የሆነ ፓርላማ ነዉ፤ የህ ፓርላማ ባለፉት 15 አመታት ከገዥዉ ፓርቲ የቀረቡለትን አያሌ ረቂቅ ህጎች ተቀብሎ አጽድቋል። በእነዚህ 15 አመታት ዉስጥ መለስ ዜናዊና ፓርላማዉ ግልፅ በሆነ መልኩ የተለያዩበት አንድም ግዜ የለም፤ እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ልብ ሊለዉ የሚገባ ነገር ቢኖር መለስ ዜናዊና ፓርላማዉ የግድ ይለያዩ የሚል እምነት የለም፤ ሆኖም በፓርላማዉ ዉስጥ የህዝብ ተወካዮች ካላቸዉ ህዝባዊና አገራዊ አደራ አንዱና ዋነኛዉ ገዥዉ ፓርቲ ወይም መለስ ዜናዊ ያሻዉን ነገር ሁሉ ለመስራት ህጋዊ ሽፋን እንዳያገኝ መከልከል ነዉ። መለስ ዜናዊና ፓርላማዉ እጅና ጓንት ሆነዉ ዝንተ ዓለም የሚስማሙ ከሆነ ግን ጥፋት ለማጥፋት ከመለስ ዜናዊ የበለጠ አጥፊ የለምና አገራችን ኢትዮጵያ ሁለት ትላልቅ አጥፊዎች አያስፈልጓትም።

የኢትዮጵያ ፓርላማ ያለዉ ስልጣንና ሐላፊነት መለስ ዜናዊ በተናጠል ካለዉ ሥልጣንና ሐላፊነት እጅግ የበለጠ ነዉ፤ ይህ ደግሞ በህገ መንግስቱ ዉስጥም የሰፈረ ሐቅ ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ የህግ አስፈፃሚዉና የህግ አዉጭዉ አካላት የስራ ግኑኝነት በህገ መንግስቱ ላይ የሰፈረና አንዱ በሌላዉ ጠባቂነት ላይ የተመሠረተ ህጋዊ ግንኙነት ነዉ እንጂ የጌታና የሎሌ ግንኙነት አይደለም። መለስ ዜናዊ ፓርላማዉን ጥያቄ ጠይቆ አግባብ ያለዉ መልስ ማግኘት እንዳለበት ሁሉ ፓርላማዉም መለስ ዜናዊን ጥያቄ ሲጠይቅ አግባብ ያለዉ መልስ ማግኘት አለበት።ከዚህ በተረፈ ግን መለስ ዜናዊ እግሩ ፓርላማዉን በረገጠ ቁጥር የሚያሰማዉ ቁጣ የተሞላበት ጩኸት "የሚገነፍል ድስት የሚያበላሸዉ እራሱን ነዉ" የሚል ተረት ያስተርትበት እንደሆነ ነዉ እንጂ ሌላ ምንም የሚያተርፍለት ነገር የለም።

መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ፓርላማ አቅርቦ ካስወሰናቸዉ ዉሳኔዎች ዉስጥ አንዱ በ1999 ዓም ሶማሊያን ለመዉረር ያስወሰነዉ ዉሳኔ ነዉ። ይህ ልበ ድፍን ሰዉ የኢትዮጵያን ዉድ ልጆች ወደ ሶማሊያ ለማዝመት የኢትዮጵያን ፓርላማ ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት ካወቀ፤ በዚያ ለሁለት አመታት በዘለቀዉ ጦርነት ዉስጥ የሞተዉንና የቆሰለዉን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ የማወቅ መብት እንዳለዉ ማወቅ አለበት። በሰለጠነዉ ዓለም የሚኖረዉ ህዝብ ልጆቹ ጦር ሜዳ ላይ ሲሰዉ ገና ደማቸዉ ሳይቀዘቅዝ ነዉ መርዶዉ የሚነገረዉ፤ ይህ ደግሞ የግድ የስልጣኔያቸዉ ምልክት ሳይሆን ለሰዉ ልጅ ህይወት ያለቸዉን ከፍተኛ ክብርና ፍቅር ነዉ የሚያሳየዉ።

የአንድን ሰዉ ፀባይም ሆነ አርቆ የማሰብ ችሎታ ሰዉየዉ በንግግሩ ዉስጥ ከሚጠቀምባቸዉ ቃላት ማወቅ ይቻላል ብለዉ የሚያምኑ ብዙ የስነ አዕምሮ ምሁራን አሉ፤እነዚህ ምሁራን ይህን እምነታቸዉን በተግባር ለማረጋገጥ ከፈለጉ ከመለስ ዜናዊ የተሻለ ሰዉ የሚያገኙ አይመስለንም። መለስ ዜናዊ ባለፉት ብዙ አመታት ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለዉን ጥላቻና ንቀት በግልፅ የሚያሳዩ ንግግሮችን ተናግሯል፤ ለምሳሌ ገና አዲስ አበባን እንደረገጠ ክቡር ባንዲራችንን እሱና ተከታዮቹ አንጠልጥለዉ ከገቡት ቆሻሻ ጨርቅ ጋር አወዳድሮታል፤ ብዙም ሳይቆይ ዓለም በቅናት የሚመለከተዉን የብዙ ሺ ዘመናት የነፃነት ታሪካችንን በ100 አመት ገድቦታል። ይህ ብቻ አይደለም! ተከታታይ የቅኝ ገዥዎች በትር ያረፈባትን አገራችን ኢትዮጵያን በቅኝ ገዢነት በመፈረጅ በተለያዩ መድረኮች ሲያወግዛት ኖሮአል :: የዛሬውን አያድርግበትና ።

የመለስ ዜናዊ ዕብሪትና ተንኮል እየባሰበት መጥቶ ዛሬ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚገባ ተገንዝቧል ብለን እናምናለን።ያልተገራ የጫካና የበረሐ ፀባዩን ተሸክሞ አዲስ አበባ የገባዉ ከሀዲዉ መለስ ዜናዊ የህዝብ ተወካዮችንና የደደቢት ጓደኞቹን ለያይቶ መመልከት ተስኖታል፤ ስለሆነም ጎንበስ ቀና እያሉ በሚሰግዱለት በነበረከት ስምኦን ላይ የሚያሳየዉን ዕብሪትና ትዕቢት ዛሬ የፓርላማዉ ዉስጥ የቀን ከቀን ድራማ አድርጎታል። በቅርቡ ፓርላማዉ ዉስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በሶማሊያዉ ጦርነት ወቅት በወገን ጦር ላይ የደረሰዉን የጉዳት መጠን ጠይቀዉ ያገኙት መልስ እንኳን ጦሩን ካዘመተዉ የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስቴር--- የወያኔ ጦር ክፉኛ ካረፈበት ከአልሸባቡ መሪ ከሐሰን ዳህርም የሚጠበቅ አይደለም። ሀፍረተ ቢሱ መለስ ዜናዊ ምን ያህል ወታደር ሞተ ተብሎ ለተጠየቀዉ ጥያቄ እንደዚህ ሲል ነበር የመለሰዉ "ይህንን የክል ሰዉ ሞተ ብዬ የመናገር ግዴታ የለብኝም፤ ደግሞም የዚህን ዝርዝር ማወቅ የእናንተ ጉዳይ አይደለም"

መለስ ዜናዊ ጥያቄ በተጠየቀ ቁጥር እየተቆጣና እየተሳደበ እስከመቼ እንደሚዘልቅ ብዙ የታወቀ ነገር ባይኖርም ይህ ዕብሪተኛ ሰዉ መረዳት ያለበት አንድ ነገር አለ፤ ይሄዉም ቁጣ፤ክፋትና ዕብሪት እንደ አሲድ ለብልበዉ የሚፈጁት በዉስጡ ያካማቻቸዉን ሰዉ ነዉ እንጂ ቁጣዉ የተነካጠረበትን ሰዉ አይደለም። መለስ ዜናዊ ጥያቄ በተጠየቀ ቁጥር ምለሹ ቁጣና ስድብ መሆን የለበትም፤ በቁጣ የተጀመረ መልስ ማሳረጊያዉ ኃፍረት ነዉና መለስ ዜናዊ በተቆጣና ህዝብን በተሳደበ ቁጥር ኃፍረቱን የሚከናነበዉ የተሰደበዉ ህዝብ ሳይሆን ተሳዳቢዉ መለስ ዜናዊ እራሱ ነዉ። በእርግጥ ቁጣና ደስታ የስሜት መግልጫዎች ናቸዉና ቁጣ ወይም ደስታ በዉስጡ የሌለበት ሰዉ ካለ ያ' ሰዉ በቁሙ የሞተ ሰዉ ነዉ፤ ነገር ግን እንደመለስ ዜናዊ በነጋ በጠባ በህዝብ ላይ የሚቆጣና ህዝብን የሚዘልፍ ሰዉ በቁም መሞቱ ብቻ ሳይሆን ቀድሞዉኑ ለመቆም መብቃቱ እጅግ ያሳዝናል። መለስ ዜናዊም ሆነ እሱ በተናገረ ቁጥር የሚያጨበጭቡለት ሆድ አፍቃሪ ምሁራን አጥብቀዉ ሊረዱት የሚገባ ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን መንግስት መጠየቅ ያለበት "ምን ይደረግልኛል" ብሎ ሳይሆን "ይህ ለምን አልተደረገልኝም" ብሎ ነዉ።ይህ ደግሞ ህዝብና መንግሰት አብረዉ እስከኖሩ ድረስ ማንም ሊሽረዉ የማይችል የህዝብ መብት ነዉ።መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ጦር ወደ ሶማሊያ ለማዝመት የህዝብ ተወካዮችን ፈቃድ የመጠየቅ ግዴታ እንዳለበት ሁሉ እነዚህ ፈቃድ የሰጡት የህዝብ ተወካዮች የሚጠይቁትን ማንኛዉንም ጥያቄ በአግባቡ የመመለስ ግዴታ እንዳለበት ማወቅ አለበት።

የኢትዮጵያ ፓርላማ ምንም ይሁን ምን የህዝብ ተወካዮች የሚገኙበት ስብስብ ነዉና ለህዝብ ካለን አክብሮትና ፍቅር የተነሳ የመለስ ዜናዊን የፓርላማ ድራማ አስመልክተን ብዙ ተናገርን እንጂ ባለፈዉ ሰሞን ፓርላማዉ ዉስጥ ለታየዉ ቅጥ ያጣ ድፍረት ተጠያቂዉ መለስ ዜናዊ ብቻ ሳይሆን ፓርላማዉም ጭምር ነዉ።የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ማንነታቸዉን ቢረዱና ተጠሪነታቸዉ ለመለስ ዜናዊ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን ቢያዉቁ ኖሮ መለስ ዜናዊን ጥያቄ ጠይቀዉ "ምንም አያገባችሁም" የሚል መልስ ባላገኙም ነበር።በተለይ እነሱ የሚወክሉት ህዝብ ልጅ ስለሆነዉና በነሱ ፈቃድ ስለዘመተዉ ሠራዊት መረጃ ጠይቀዉ አያገባችሁም ሲባሉ በዝምታ አንገታቸዉን መድፋታቸዉ ቀድሞዉኑም ቢሆን ፓርላማ የገቡት ለህዝብ ለመስራት ሳይሆን መለስ ዜናዊን ለማጀብ መሆኑን ያመለክታል። የአንድ ሰዉ ወይም ደርጅት ክብርና ማንነት በጋጠወጦች ሊጠቃ፤ሊሰደብና ሊቀለድበት ይችል ይሆናል፤ ሆኖም ጋጠወጦች ሊያስሩንና ሊገድሉን እንጂ ክብራችንንና ፈቃዳችንን በገዛ እጃችን ካላስረከብናቸዉ በቀር እነሱ በፍፁም ሊቀሙን አይችሉም። የኢትዮጵያ ፓርላማ አባላት እንደዚያ የተደፈሩት እነሱነታቸዉን፤ መብታቸዉንና ክብራቸዉን ለጋጠወጦች አሳልፈዉ ስለሰጡ ነዉ።

መለስ ዜናዊ እሱ እራሱ ፀረህዝብ ነዉና የህዝብ ተወካዮችን ላይወዳቸዉ ይችላል ያ' የራሱ ጉዳይ ነዉ፤ የህዝብ ተወካዮችን ማክበርና የሚሉትን መስማት ግን ግዴታዉ ነዉ።ፓርላማዉ ዉስጥ የመለስ ዜናዊና የህዝብ ተወካዮች መስማማት፤በጋራ መስራትና መተባበር ትልቅ ነገር ነዉ :: ከሁሉም በላይ ግን በአብሮ መስራት ዉስጥ ሊከሰት የሚችለዉን የሀሳብ ልዩነት ማክበር ከትልቅነት ሁሉ የላቀ ትልቅነት ነዉ።ኃይል አልባ የሆነ ህግና ህግ የማይገዛዉ ኃይል ሁለቱም የስርዐተ አልበኝነት ምልክቶች ናቸዉ፤ ስለሆነም መለስ ዜናዊ የህግ አስፈፃሚዉ አካል የበላይ ነዉና አንዳንዴ አግባብ ባለዉ መልኩ ኃይል መጠቀም ይችላል ሆኖም ይህ የሚጠቀመዉ `ኃይል ህጉ ከሚፈቅድለት በላይ ሊሆን አይገባም።

በኛ ግምት የአገሩን ሉአላዊነት ላለማስደፈር በተጠንቀቅ የቆመዉ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ይገነዘበዋል ብለን የምናምነዉ አንድ ትልቅ አገራዊ ሐቅ አለ፤ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ታሪካዊ ሐላፊነትና ተጠሪነት ለአገርና ለህዝብ ነዉ እንጂ በየወቅቱ ስማቸዉን እየቀያየሩ ለሚመጡ መንግስታት አይደለም። በእርግጥ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የአገሪቱ ህገ መንግስት በዘላቂነት መከበሩን የሚጠባበቅ ኃይል ነዉ፤ ህገ መንግስት ደግሞ መንግስት እንዳሰኘዉ እየዘለለ ህዝብን እንዳይራገጥ ህዝብ መንግስትን የሚለጉምበት ልጓም ነዉ እንጂ መንግስት ህዝብን የሚያፍንበት መሳሪያ አይደለም። ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የወጣዉ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ለግዳጅ በሚላክበት ግዜ የሠራዊቱ እናትና አባት በልጃቸዉ ብሄራዊ ተልዕኮ ቢኮሩም ተልዕኮዉ ሞትን ያክል ትልቅ መስዋዕትነት አለበትና ልጃቸዉ ጦር ሜዳ ሲዘምት የነሱም ልብ አብሮ ይዘምታል። ይህ ከልጃቸዉ ጋር የዘመተዉ ልብ ልጃቸዉ ከተመለሰ አብሮ ይመለሳል አለዚያም እንደዋለለ ይቀራል።ይህንን የሚዋልል የእናትና የአባት ልብ ለማሳረፍ ነበር ባለፈዉ ሰሞን አንዳንድ የፓርላማዉ አባላት በሶማሊያዉ ጦርነት የተሰዉትን የኢትዮጵያ ወታደሮች ቁጥርና ማንነት ለህዝብና ለቤተሰቦቻቸዉ እንዲገለጽ የጠየቁት። የህዝብና የአገር ፍቅር በደም ሥሩ የሌለበት መለስ ዜናዊ ግን ወጣቶችን ከወላጆቻቸዉ ጉያ እየሳበ ማዝመት ነዉ እንጂ ከዘመቱ በኋላ ይድላቸዉ ይክፋቸዉ ወይም ይኑሩ አይኑሩ እሱ የሚቸግረዉ ነገር የለም።

በየቀኑ ካለማቋረጥ የሚፈሰዉን የኢትዮጵያ ህዝብ እምባ በአጭር ግዜ ዉስጥ ለአንዴም ለመጨረሻም ግዜ ለማስቆምና ህዝብ እንደገና እንዳያለቅስ የማድረግ ችሎታ ካላቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች ዉስጥ አንዱ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ነዉ።የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዉያንን ከሚንቁና ከሚረግጡ ኃይሎች ጋር ከዚህ ቀደም እንዳልተባበረና እንዳላቀፋቸዉ ሁሉ ዛሬም ለወደፊትም አይተባበርም አያቅፋቸዉምም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሠራዊቱ አያት ቅድመ አያቶቹ በደማቸዉ ያስከበሩትን የኢትዮጵያ ዳር ድንበር እንደ ዋዛ የሚመለከትንና የሚመራውን አገር ዜጎች በውክልና ጦርነት ውስጥ ማግዶ ውድ የሆነ የህይወትና የአካል ዋጋ ካስከፈለ ቦኋላ ሰለሟቾች የጠየቁትን የህዝብ ተወካዮች "ምንም አያገባችሁም" የሚልን የአገር መሪ ድምፁንና ኃይሉን አስተባብሮ "አንተ ለአገር አታስፈልግም" ማለት መቻል አለበት። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አገርንና ህዝብን የሚከላከለዉ ከዉጭም ከዉስጥም ጠላቶች መሆን ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ዉስጥ ሠላም፤ እኩልነትና መከባበር የሚሰፍነዉ እንደ መለስ ዜናዊ አይነቶቹ የአገርና የህዝብ ነቀርሳዎች ተወግደው በምትካቸው በነጻ ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት የሚቋቋም መንግስት እንዲኖረን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው።

## የታዋቂው የሙዚቃ ንጉስ ጥላሁን ገሰሰ ቀብር (ከገጽ 1 ገስ የዞረ)

ናቸው። የተቀበረን የሃገር ፍቅር ስሜት ፈንቅለው የማይቀሰቅሱበት ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊ የለም። በተለይ "ኢትዮጵያ" የተሰኘውን ታዋቂውን ዜማውን ከብሔራዊ መዝሙር ጋር የሚያሳስተው ሳይኖር አይቀርም። ይህ በሃገር ፍቅር ስሜት የሚያሰክረው ግጥም እና ልብን በደስታ የሚያፍለቀልቅ ዜማ ራድዮኑ ላይ በመጣ ቁጥር፣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በወኔ ገንፍሎ ሃገርን በመታደግ ስሜት ይሞላል።

ጥላሁን ገሠሠ፥ ይህንን ወደ ህዝብ ልብ ጠልቆ በመግባት የማነሳሳት ተሰጥውን ተጠቅሞም፣ በ1960ዎቹ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩት በረሃብ የተጠቁ ዜጎች ድምጽ ሆኖ የእርዳታ እጆችን አነሳስቷል። ያኔ እምባ ፊቱን እያጠበው ያንጎራጎረው፥ "ዋይ ዋይ ዋይ ሲሉ፣ የረሃብን ጉንፋን ሲስሉ" የተሰኘው ዜማው ዛሬም ቢሆን ማስለቀሱ አልቀረም።

ውዱ ድምፃዊ፥ ስለ ፍቅር፣ ስለ ትዝታ፣ ስለ ሃዘን፣ ስለ ናፍቆት ስለ ደስታ፣ ስለመለያየት አቀንቅኖልን፤ ጊዜ የማያስረጃቸውን ብርቅዬ አስተዋጽዎች ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ጥሎ ሄዷል። ለረሃባችን ድምጹን እንደለገሰ ሁሉ፣ "ሰው ፍቅርን ካገኘ ምግብማ ሞልቷል" በማለት፣ እንዲሁም ለእርዛታችንም ቢሆን "የፍቅርን ሸማ መደረብ" እንደሚቻል በማቀንቀን፣ በመቀራረብ ውስጥ ስላለው የአሸናፊነት ሚስጥር ሊያስተምረን ሞክሯል።

ጥላሁንንስ አንረሳውም፤ እንርሳው ብንል እንኳ አይሆንልንም። "ትንፋሼ ተቀርጾ ይቀመጥ ማልቀሻ፣ እንዳው የሞትኩኝ ለት ለኔ ማስታወሻ" ብሎን የለ? ይልቁንስ እንመኝ እስኪ፥ እንደ ጥላሁን ፋና ወጊዎች፣ መልካም አሻራ ጥለን የምንሄድ ብሩክ ትውልድ ያድርገን።

ዛሬ፥ በዓለም ዙሪያ ላለን የጥላሁን አድናቂዎች፣ አፍቃሪዎች እና አክባሪዎች፣ "ፊታችን በእንባ ይታጠብ" ዘንድ ተራችን ነው። ደህና ሰንብት ጥላሁን ገሠሠ፤ ደህና ሰንብት አበባችን።

በተያያዘ ዜና በብርቅየው የአገር ልጅ ድንገተኛ  ሞት ህዝብ የተሰማውን አስተያየት ለማወቅ አንዳንድ ሰዎች ማነጋገሩን የገለጸው የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ እንዳስተላለፈው፣ መለስ ዜናዊ የሃዘን መግለጫ ለሚች ቤተሰብ ማስተላለፉ ከተሰማበት ሰዓት ጀምሮ ከፍተኛ የህዝብ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ቆይቷል። ዘጋቢያችን በዚህ ጉዳይ ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪ፥ "የአገዛዙ ቁንጮ መለስ ዜናዊ፥ እንኳን የአንድ ግለሰብ፣ የአገር ሞት ደንታ አይሰጠውም። በተለይ ደግሞ፥ ወያኔ ጫካ በነበረበት ወቅት ያለመውን እና አሁን ሥልጣን ከያዘ በኋላ እውን ሊያደርግ የሚሞክረውን አገር የማፍረስ ህልም ለማክሸፍ ይደረግ በነበረው ጦርነት፣ "አሳደህ በለው ያንን ወንበዴ......." በሚለው ዜማው ጦር ግንባር ድረስ ተጉዞ የሰራዊቱን ወኔ ሲቀሰቅስ ለነበረ አገር ወዳድ ዜጋ ከምር ሊያዝን የሚችል ልብ የለውም። ለዚህም ባለፉት 19 ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ የታየው፣ ከቂምና ከበቀል የጸዳ አዕምሮ እንደሌለው ያረጋገጠው ባህሪይው ምስክር ነው፤" ብለዋል። ዘጋቢያችን ጨምሮም፥ ብዙዎች ይህ የመለስ ስራ በዚህ መሪር ሃዘን የተሰበረውን የህዝባችንን አንጀት በመብላት የተለመደውን ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የታሰበ ከመሆን አያልፍም የሚል እምነት እንደሚያንጸባርቁ ገልጿል።

መለስ ዜናዊ ስልጣን ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ የአገሪቷን ታሪክ በማንቋሸሽ እና የአገሪቷን ዳር ድንበር ለባዕድ አሳልፎ በመስጠት ለህዝብ ያለውን ንቀት በተደጋጋሚ ያሳየ፤ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ለመደፍጠጥ ሲል በተለያዩ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ጭምር የተረጋገጠ ወንጀል በክቡር የሰው ልጆች ላይ የፈጸመ፤ በደሃው ህዝብ ሥም ተለምኖ የሚገኝ ገንዘብ በራሱና በባልሥልጣኖቹ ስም እየዘረፈ አገሪቱ በታሪኳ ገጥሟት የማይታወቅ ሙስና ውስጥ የዘፈቀ ሰው ነው። የስልጣን እድሜውን የሚያራዝም በሚመስለው ጉዳይ ላይም የአገሪቷን ጥቅም ለምንም አሳልፎ ከመስጠት ወደ ኋላ የማይመለስ  እንደሆነ በስልጣን ላይ በቆየባቸው አመታት ታይቷል።

ጥላሁን ገሰሰ ከግማሽ  ምዕተ አመት በላይ  ሳያሰልስ ስለ ሃገሩ እና ስለ ህዝቡ በፍቅር ያዜመ እና የህዝቡ መቸገር የሚገደው ቅን ዜጋ እንደነበር ይታወቃል። የዝነኛው አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሰሰ የቀብር ሥነሥርዓት ዛሬ ወዳጅ ዘመዶቹና በርካታ አፍቃሪዎቹ በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይፈጸማል።



## ወያኔ በብቸኛ ተዋናይነት የሚጨፍርበትን የ"ምርጫ" ተብዬ መድረክ ለመፍጠር ላይ ታቹን ተያይዞታል:: የቀድሞውን ዋና ተዋናይ በረከትን በመተካት መለስ እራሱ ገብቶበታል::

ተቃዋሚ ፓርቲዎች እጅ ከወርች በታሰሩበትና ባለፈው ምርጫ 97 የታየውን የምርጫ ውጤት አስመልክቶ በህዝባችን ላይ የተፈጸመው አሰቃቂና ዘግናኝ ሰቆቃ ከዜጎች አዕምሮ ሳይደበዝዝ ወይም ዳግም ላይደገም ምንም ማረጋገጫ ሳይሰጥ የወያኔ ቁንጮዎችና አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰለ ቀጣዩ ምርጫ ዘመቻ ከአሁኑ እንቅልፍ ማጣት መጀመራቸውን የወያኔ መገናኛ ብዙሃን በየእለቱ ከተጠመዱበት የፕሮፖጋንዳ ሥራ ለማረጋገጥ ተችሎአል::

በመንግሥት ሥራ የተሰማሩትን ሠራተኞች፣ መምህራን፤ ወጣቶች እና ሴቶችን በከፍተኛ የውሎ አበል ክፍያ ወደ መናገሻ ከተማው በማጓጓዝ ሰለ ወያኔ ልማታዊ መንግሥትነት ሲሰብክ የነበረው መለስ ዜናዊ ካለፈው ወር ጀምሮ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች በመጓዝ ሰለቀጣዮቹ የልማት ዕቅዶች የተለመደ ድስኩር ማድረግ ጀምሮአል :: በከምባታና ጠምባሮ ባደረገው ጉብኝት ወቅት እንዲገናኙት በጥንቃቄ ከተመለመሉት አንዱ በምርጫ 97 ወቅት ህዝቡ ተሳስቶ ቅንጅትን በመምረጡ በበቂ ሁኔታ እንደተቀጣና ከቅጣቱ ከበቂ በላይ የሆነ ትምህርት ያገኘ በመሆኑ ይቅርታ እንዲደረግላቸው በህዝቡ ስም ሲማጠን የፈረደበት የኢትዮጵያ ተለቪዥን ለዕይታ ማብቃቱ ይታወሳል :: መለስ ዜናዊም ወያኔ ለህዝቡ በፈጠረው የዲሞክራሲ መብት ተነሳስቶ  የመሳሳት መብቱን እንደተጠቀመና ዋናው ቁምነገር ለወደፊት እንደዚያ አይነት ስህተት ለመድገም አለመሞከር እንደሆነ አጽንኦት ሰጥቶ ሲናገር መደመጡን ;  ይህ ድግሞ በምርጫ ተብዬው የ2002 ዓም ድራማ ውስጥ ገብተው አድማቂ ለመሆን እየተንደረደሩ ላሉ ፖለቲካ ድርጅቶች ከፍተኛ መልዕክት እንዳስተላለፈ በወቅቱ የግንቦት 7 ድምጽ ዘግቦታል ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፈው አርብ ሚያዝያ 9 ቀን 2001 ዘረኛው መለስ ዘናዊ ከልጅነት የጫካ ዘመኑ ጅምሮ እጅግ አምርሮ በሚጠላው እና የመንግሥት ሥልጣን ከተቆናጠጠ ጊዜም ቦኋላ  በማንነቱ ብቻ አንገቱን ለማስደፋት ግልጽና ሥውር ቅስቀሳዎችን የከፈተበትን የአማራ ህዝብ ድጋፍ ለመሻት ወደ ሰሜን ሸዋ
እንደተጓዘና በህዝብ መካከል ተገኝቶ የንጹህ ውሀ ተጠቃሚ አደርጋችሓለሁ፤

ስርጭት እንዲስተካከል አደርግላችኋለሁ ብሎ የለመደውን የቅጥፈት መደለያ ሲደረድር ውሎ እንደተመለሰ ለማወቅ ተችሎአል :: ከራሱ አብራክ የወጡትን ጭምር በዕለታዊ ጥቅምና በተለያዩ መደለያዎች  በመግዛት ላለፉት 19 አመታት ከፍተኛ የጠላትነት ፕሮፖጋንዳ እንደተካሄደበት ሊዘነጋ የማይችለው የአካባቢው ህዝብ የመለስን በመካከላቸው ተገኝቶ የተለመደውን ዲስኩር ማድረግ ከቁብ እንደማይቆጠረው የወያኔ ቁንጮዎች አሳምረው ያወቁታል ያለው የግንቦት 7 ዘጋቢ በቦታው ተገኘተው መለስን ማታለያ እንዲያዳምጡ የተጠሩት የመንዝ ጌራምድር፤ ግሼ ራቤል፤ መንዝ ማማ፤ መንዝቀያና መንዝላሎ ወረዳ ነዋሪዎች እና ገበሬዎች የሞቀ ጭብጨባ በመንሳት ያላቸውን ተቃዉሞ አሳይተዋል  በማለት ከስፍራው ባስተላለፈው ዜና ገልጾአል :: አያይዞም ህዝቡ የመለስን የቀቢጸ ተስፋ ቃል ከቁብ ባለመቁጠር በስብሰባው ወቅት ምንም አይነት አሰተያየት ከመስጠትና ጥያቄ ከመጠየቅ ተቆጠቦ እንደነበረ ይህም ከመለስ ጋር ወደሥፍራው የተጓዙትን የአካባቢው ሰዎች ጭምር እንዳስደነገጠ ገልጾአል ::


# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።


**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።

g7radio@ginbot7.org